# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፡፡” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. /// አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

ግንቦት 1996 May 2004 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡” (ኢሳ 54÷13)

አዘጋጅ ፡- መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

**“ከራሳችሁም አንዲት ፀጉር ስንኳ አትጠፋም፤ በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፡፡** (የሉቃስ ወንጌል 21÷18-19)

## “በእምነትምና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ÷ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን፡፡”

(ወደ ዕብራውያን 6÷11-12)

ሕይወት ሀዘንና ደስታ የሚፈራረቁበት ጠመዝማዛ ጐዳና ነው፡፡ ምኞታችንና ፍላጎታችን አብዛኛውን ጊዜ በቀላሉ አይከናወንም፡፡ ብዙ ፈተና በትዕግሥት ማለፍን ይጠይቃል፡፡ በዚህም ምክንያት መታወክ÷ይልቁንም ተስፋ መቁረጥ ፈጥኖ ሊሰማ ይችላል፡፡ በአገልግሎት ወይም በሕይወትና በኑሮ ሌትና ቀን የተለፋበት ነገር በተመኘንበት ወቅት ውጤቱን ሳያሳይ ሲቀር፡- አሁንስ ተስፋ የለኝም፡- ርግፍ አድርጌ ልተወው ሊያሰኝ ይችላል፡፡ በምናልፍበት በማንኛውም የኑሮ ዘርፍ፡- በአገልግሎት÷ በቤተሰብ÷ በሥራ መስክ ሆነ በማሕበራዊ ኑሮ ይህ የማቀር ክስተት ነው፡፡

ይሁን እንጂ፡- ጌታ እግዚአብሔር አምላክህ የልፋትህን ፍሬ እስክያስጨብጥህ ድረስ የምትሮጥበትን ጸጋና ዕምነት ሊሰጥህ ዝግጁ ነው፡፡ የምታልፍበትን ሁኔታ የሚሰማህንም ስሜት÷ ጌታ ያውቃል፡፡ ቶሎም ተስፋህን እንድትጨብጥ በአባታዊ ፍቅሩ ይጠባበቃል፡፡ እንዲህም ይለሃል፡-

**“ሥራህን÷ጥረትህን÷ትዕግሥትህን አውቃለሁ፤ክፉዎችን፡ልትታገሣቸው፡እንዳልፈቀድህ÷…አውቃለሁ፡፡ በትዕግሥት፡መጽናትህንና፡ስለ፡ስሜም፡ሳትሰለች፡መከራ፡መቀበልህን፡አውቃለሁ፤”** (የዮሐንስ ራዕይ 2÷2-3)

ስለዚህ “ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል÷ እርሱም ይደግፍሃል ፤ ለፃድቁም የዘላለም ሁከትን አይሰጠውም፡፡ (መዝሙረ ዳዊት 55÷22)

ከመከራው ብርታት የተነሣ የማያልፍ ሲመስል፡- ከጨለማው ድቅድቅነት የተነሣ የማይነጋ መስሎ ሲያስፈራራ፡- የተስፋና የዕምነት ጭላጭል ሲመነምን ምን ይደረጋል? ሕዝብ በሞላበት ከተማ እየኖረ በብቸኝነት ተውጦ÷ ምኞቱ በመዘግየቱ ተስፋ መቁረጥ ደጁን የሚያንኳኳበት ሰው ምን ምክር አለለት?

የሚከተለው የእግዚአብሔር ባሪያና የሕዝቡ መምሕርት የሆነች ታዋቂዋ ጂል ብርስኮ ከጻፈችው Faith Enough to Finish ከተባለው መጽሐፍ በተወሰደ መልዕክት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ምክር ነው፡፡

## እስከ ፍጻሜ የሚያጸና ዕምነት

ዛሬ በሕይወት መኖርህ ዓላማ ያለውና ክቡር መሆኑን አስተውል። የሕይወትንም ዓላማ የሰጠህ እግዚአብሔር፡- አስፈላጊውን ጸጋና ርዳታ በየወቅቱ ሊሰጥህ ከጐንህ ፈጽሞ እንደማይለይ ዕመን። *(አስተውል፥ ዕምነት እንጂ ስሜት አይደለም። ምክንያቱም በመከራ ወቀት የጌታ ቀርበት ላይሰማ ስለሚችል ነው።)* በየዕለቱ የሚያስፈልግህን ብርታት እንዲሠጥህ ወደ ጌታ ጸልይ። እያንዳንዱን ዕለት ሆን ብለህ በተስፋና በቀና አዕምሮ በመቀበል በዕለቱ እንድትለማመድ የጌታ ፈቃድ የሆነውን ሁሉ ፈጽመህ ለመዋል ድፈር።

ስለ ችግርህ በእግዚአብሔር ላይ አታጉረምርም። ምክንያቱም *(በያዕቆብ 1፥13)* “… እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም፡፡” ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው። ነገር ግን በዚህ በኃጢአተኛ “ዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ” እንዳለው ስለ ሆነ በተለያዩ መከራዎች ውስጥ እንድናልፍ ይፈቀዳል። እርሱም በሐዘናችን አብሮን ያዝናል። ይሁን እንጂ ስለ ጽድቅ በዕምነት የምንጋፈጣቸውን መከራዎች፥እንደ ወርቅ አንጥሮ ሊያጠራን ስለሚጠቀምባቸው መከራን እንድንታገሥ ይመክረናል። ስለዚህ የመከራህን ስሜት ሳታስተባብል ግለጽለት። ከዚያም እንደሚረዳህ በእግዚአብሔር ታመን።

ሰዎችና ሁኔታዎች በየጊዜው ይለወጣሉ እግዚአብሔር ግን አይለወጥም ፥ አያዳላም። “እየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው። *(ዕብራውያን 13፥8)* “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም፡፡” *(ማቴዎስ 24፥35)*

ምሕረቱን ተቀበል።ኃጢአትህን ተናዘዝ ንስሐ ግባ፡- ወደፊት ጸጋው በሚያስችልህ መጠን በንጽሕና ኑር። ዛሬ በደረስህበት በሙላት ተመላለስ። በተረፈ ግን ስላለፈውም ሆነ ስለሚመጣው ነገር ራስህን ያለ አግባብ ከመኮነን ተጠበቅ።

“በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል፡፡” *(ምሳሌ 3፥5-6)* አምላክህ እግዚአብሔር፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ ሁሉን የሚችል፥በሁሉም ሥፍራ ሊገኝ የሚችል ታላቅ አምላክ መሆኑንና ስለ አንተ እንደሚገደው በማስተዋል ኑር። እርሱ የሚሻልህን በእርግጥ ስለሚያቀና ካለህበት መከራ መውጫውን ስለሚያውቅ፡- ለሕይወትህ ምሪት አዘውትረህ ፀልይ፤ ከዚያም ድምፁን ለመስማት በትጋት አድምጥ። “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፥ እኔም አውቃቸዋለሁ፥ ይከተሉኝማል፤” ያለውን ተለማመድ። *(የዮሐንስ ወንጌል 10፥27)*

ጥሪህን ዕወቅ። የማንኛውም ክርስቲያን ተቀዳሚ የሕይወት ጥሪ የእግዚአብሔር ታማኝ ወዳጅ መሆን ነው። በአንተ ውስጥ ያስቀመጠውን ልዩ መክሊት በመጠቀም እርሱን ማገልገልህ ከዚያ ቀጥሎ የሚሆን ጉዳይ ነው። ስለዚህ፡- ጊዜህን፥ ጉልበትህን፥ልብህንና ገንዘብህን የምታውልበትን ነገር በማስተዋል አድርግ።

እግዚአብሔርን እንደ ታላቅ የሕይወት ግምበኛ አስበው። እርሱም በሕይወትህ የሚያጋጥሙህን ነገሮችና ሰዎች ፡- እንደ መዶሻ፥እንደ መጋዝና ሞረድ በመጠቀም ልጁን እስክትመስልለት ድረስ ያበጅሃል። መዶሻው ሲጉሽምህ፥ መጋዙ ሲገዘግዝህ ወይም ስትሞረድ፡- ሊያስተካክልህ፥ ሊያጠራህና ሊያሳምርህ እንጂ ሊጎዳህ እንዳልሆነ በማወቅ ታገሥ።ይልቁንም ዘወትር በጌታ እጅ ለመበጀት በፈቃደኝነት ዝግጁ ሁን።

መጽሐፍ ቅዱስህን በየዕለቱ በማንበብ የጥሞና ጊዜ (meditate ቃሉን ማሰላሰል) ይኑርህ። መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በመጠቀም የሰዎችን ሕይወት መለወጥ ተግባሩ ስለ ሆነ፥ ያለ ቃሉም ሊረዳህ ስለማይመቸው፥ በቃሉ እንዲያንጽህ ለምን።

ደፋር ሁን። ጌታ አንዳንድ ጊዜ ለራስህም ሆነ ለሚቀርቡህ ሰዎች የማይመች ነገር እንድታደርግለት ይጠይቀሃል። ስለዚህ እርሱን በታማኝነት ማገልገል ዋጋ ያስከፍላል።በእርሱ ላይ ማመፅም ዋጋ ያስከፍላል። አመፃ ያዋርዳል። በመታዘዝ የሚከፈለው ዋጋ ግን እጥፍ ብድራት አለው።

ጌታ ለሚያዝህ ነገር ሁሉ ችሎታውንም ያዘጋጃል። አንተ ብቻ ደፋር፥ ታማኝና ታዛዥ ከሆንህ፡- እንደ አብርሃም እንደ ነብያትና እንደ ሐዋሪያት ለሰዎች ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር በመዋል ለራስህም አክሊል ታተርፋለህ።

ዕምነትህንና ለእግዚአብሔር መንግሥት ያለህን ድርሻ አትናቅ፤ጌታ በትክክል አንተን ሊተካ የሚችል ያንተ ቅጅ የሆነ ሌላ ሰው ስላልፈጠረ፡- በጥሪህ ታዘዝ፡ ባትታዘዝ ግን በአንተ ፋንታ የሚነሣው ሰው በሙላት ሊተካህ ስለማይችል፡- በፍርድ ቀን ታፍራለህ፡፡

እግዚአብሔርን ማገልገል ሰዎችን በማገልገል ነው፡፡ ስለዚህ ጸጋው በበዛልህ መጠን ሰዎችን አገልግል። ከመክሊትህና ጥሪህ ጋር በሚሄዱ አገልግሎቶች ውስጥ በውዴታ ተሳተፍ። በአደባባይ ቢሆን ወይ በስውር፡- ታማኝ አገልግሎትህ ከጌታ ፊት እንደማይሰወር ተረዳ። በአጋጣሚዎች ሁሉ፥በዛም አነሰ፥ የክርስቶስን ፍቅር ለሰዎች ማካፈል ልማድ ይሁንልህ።

በሰዎች ላይ ተስፋ አትቁረጥ። ፈጽሞ አይድኑም የተባሉት ሲድኑ፥ አይረቡም የተባሉት ልጆች፥ ባሎች፥ ሚስቶችና ወላጆች ተለውጠው፡-ለእግዚአብሔር ክብር ሲቆሙ ደጋግሞ ታይቶአል። አይሆንም የምትለው ነገር በጊዜው ሆኖ፥ዛሬ ሲታይ የማያልፉ የሚመስሉ መከራዎችም በሰዓታቸው አልፈው ታገኛቸዋለህ። ስለዚህ አይዞህ። በሕይወት፥በአገልግሎት ሆነ በኑሮ፡- መከራ ማለፋ ስለማይቀር በርታ!! ጽና!!

“በእግዚአብሔር የምታምኑ ሁላችሁ፥በርቱ፥ ልባችሁም ይጥና፡፡” *(መዝሙር 31፥24)*

“የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜ መንገድህ ይቀናልሃል፤ይከናወንልሃልም። **በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ፤ አትፍራ፥ አትደንግጥም ብዬ አላዘዝሁህምን?”** *(መ/ኢያሱ 1፥8-9)*

■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■■

“አሁንም÷እነሆ÷እግዚአብሔር ለመቅደስ የሚሆን ቤትን ትሠራ ዘንድ መርጦሃልና ጠንክረህ ፈጽመው::” (1ኛ ዜና 28÷10)

ውድ “ከእግዚአብሔር ፍቅር” ደብዳቤ አዘጋጅ:- በጌታ በየሱስ ስም ሰላምታዬን አስቀድማለሁ:: ...የደብዳቤው መልዕክት ለዘመናችንና ለትውልዱ ከፍተኛ ምክር÷ትምሕርትና መጽናናት የሚሰጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: አዘጋጆቹን እግዚአብሔር አምላካችን ይባርክ::

ውድ አዘጋጅ:- ከደብዳቤአችሁ ስለ ተማርሁና ስለተባረክሁበት እኔም አምላኬ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ በግጥም ለመደገፍ ሁለት ግጥሞች ልኬአለሁ::



## ከውኃው አትውጪ

ከተወሰነልሽ ከሚስማማሽ ሠፈር
ከሚመችሽ ቦታ ከዚያ ትልቅ ባሕር
ደልቶሽ ተከልለሽ ከተቀመጥሽበት
መሻትሽን ሁሉ ከምታገኚበት
ዓሢት እንዳትወጪ ከዚያ ካንቺ ሥፍራ
ውጪው ላንቺ አይሆንም ላንቺም አልተሠራ::

ከመኖሪያሽ ሥፍራ መረቡን ዘርግተው
ይጠባበቃሉ መውጣትሽን ከውኃው
ሙት ካረጉሽ ኋላ ከውኃው አውጥተው
ይቀራመጡሻል አንቺን ለምግባቸው::

ይህንን ስለማውቅ: እንደሚተጉብሽ
አንቺ÷ ዓሣ ስሚኝ: ቅን ምክሬን ላካፍልሽ
በመረቡ ስፋት ሳትደናገጪ
ከያዝሽውም ሥፍራ ከመስመር ሳትወጪ
ዘወትር ተከልለሽ ከወጥመዱ ርቀሽ
ከውኃው አትውጪ ኑሪ በዚያው ጸንተሽ::

በድንገት ተይዘሽ: የወጣሽ እንደ ሆን
ዓሣ: ትዋጫለሽ: ታጪአለሽ ሕይወትሽን
ስለዚህ ዘወትር በማስተዋል ሆነሽ
ከሚያሳድዱሽ ነቅተሽ ተጠብቀሽ
ከሕይወትሽ ባሕር ከሚደላሽ ቦታ
አመስግነሽ ኑሪ ዘወትር በእርጋታ::

ብዬ ባናግራት ዓሣዋም መለሰች
የልቧን አውጥታ እንዲህ ተናገረች

ውኃዬ ነውና ምግቤ መኖሪያዬ
ዘወትር የሚያጠጣኝ ሁሌም እርካታዬ
የሕይወቴን ውኃ እርሱን መርጬአለሁ
በእርሱ ተሸሽጌ ከአጥማጁ አመልጣለሁ
ከሌሎች ሥፍራዎች ይኸ ይሻለኛል
ሕይወት የሚሠጠኝ እርሱ ተስማምቶኛል::

ማረፊያ መንግሥቱ
(ኦለታ÷ ካንሳስ USA)

---

እህታችን ማረፊያ÷ ውብና ጣፋጭ ግጥም ነው:: በርቺ:: አዘውትረሽ ጻፊ:: ጽሑፎችሽንም ሁሉ በጥንቃቄ አኑሪ:: ምን ጊዜም የጽሑፍሽን ዋና ቅጅ ለራስሽ ማስቀረት አትርሺ:: ጌታ ይባርክሽ::

**የደብዳቤአችን አቀራቀረብ:-** በቀላሉ የሚባዛ÷በቶሎ የሚነበብ÷በኪስ የሚያዝ÷አባዝቶ በቤተ ክርስቲያን ደጃፍና የእኛ ሰው በሚገበይባቸው ሱቆች ለማስቀመጥ የሚመች መሆኑ:- የጌታን ቃል ለማስፋፋት በተለይ ምቹ ያደርገዋል:: ይህንን ያስተዋላችሁ እንዳላችሁ እናውቃለን:: መንፈስ ቅዱስ በሚያሳስባችሁ ሁሉ ከመተባበር አትቆጠቡ:: ጌታ የሚናገራችሁ እንዳላችሁ ስለምናምን ማሳሰባችን ነው:: እየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርካችሁ::

## “ከተደባለቀ” (ማቴ 5÷13)

ለጣዕመ ቢሱ አጣፋጭነቱን
ተፈላጊ ቅመም ጣዕም ሰጪነቱን
ከቶ ሳይረዳው እንዲሁ ከኖረ
እንደ ርካሽ ነገር ራሱን ከቆጠረ
አልጫ በመሆን ባሕሪዩን ካስናቀ
ከእነ አሸዋ ጋራ ከተደባለቀ
ገብቶ እንደ ማጣፈጥ መሬት ከወደቀ
አቤት ጨው ሲያሳዝን ራሱን ካላወቀ!

ማረፊያ መንግሥቱ

# WWW.

ethioGodslove.org

የዓለም አቀፍ ድር አገልግሎታችንን ጎብኙ:: ምርጥ መዝሙሮችን እያዳመጣችሁ÷ የአማርኛ መልዕክቶቻችንን አንብቡ::

የመዝሙር ምርጫ÷አስተያየትና ምክር እንቀበላለን:: ጌታ ይባርካችሁ::

# የሕይወት መዝገብ

“ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል” (ማቴዎስ 12÷36)

“ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለችና ዛፍዋን መልካም÷ፍሬዋንም መልካም አድርጉ÷ወይም ዛፍዋን ክፉ ፍሬዋንም ክፉ አድርጉ:: እናንተ የእፉኝት ልጆች÷ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና:: መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል÷ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል:: እኔ እላችኋለሁ÷ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና: ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ::” (ማቴዎስ 12÷33-37)

ከመጽፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የሕይወት መጽሐፍ የሚባል መዝገብ በእግዚአብሔር ዘንድ አለ:: እርሱም ጌታችንን እየሱስ ክርስቶስን አምነውና ተቀብለው የሚያመልኩት÷ የመንግሥተ ሰማይ ወራሾች ስም ዝርዝር የተመዘገበበት መጽሐፍ ነው:: ሌላ መጽሐፍ የሚባል በራዕይ 20÷12 ላይ የተጠቀሰም አለ:: ይህም የሚያሰረዳን:- እግዚአብሔርን የሚያመልኩትና የማያመልኩት ሁሉ በየዕለቱ የሚያደርጉት÷ የሚናገሩትና የሚያስቡት ሁሉ የሚመዘገብ መሆኑን ነው:: ይህም ከሆነ ሁሉም ሰው በምድራዊ ዘመኑ ስላሳለፈው ሕይወቱና አኗኗሩ÷ ስለ እያንዳንዱ ዕለት÷ ተጠያቂ ነው::

መጽሐፋችን በዕብራውያን 10÷27ና 28 እንዲህ ይላል:: <u>“ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት: ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበላቸው</u>÷ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ÷ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታያቸዋል”ይላል:: ይህ ምን ማለት ነው?

እግዚአብሔርን በመፍራት መኖርና አለመኖራችን ይመዘገባል:: ሰዎች አዩን አላዩን እያልን የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ይመዘገባሉ:: የሚሰማኝ የለም በማለት የምንናገረው ሁሉ ይመዘገባል:: እግዚአብሔርን ማምለክ እንደ ከንቱ መቁጠራችን ይመዘገባል:: መጽሐፍ የሚለውን እንመልከት:-

“ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ÷ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ:እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጽሐፍ ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ::” (ራዕይ 20÷12)

በሰማያዊው መዝገብ (በሕይወት መጽሐፍ) ከሚመዘገቡት ነገሮች አንዱና ዋናው የስሞች ዝርዝር ነው:: በዚያ መጽሐፍ ውስጥ መመዝገብን ችላ ማለት ለዘላለም መሰቃየትን ያስከትላል:: ምክንያቱም “በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ::” ስለሚል ነው(ራዕይ 20÷15)

በሕይወት መጽሐፍ ለመመዝገብ የጌታ እየሱስ ክርቶስን የግል አዳኝነት አምኖ በመቀበል ያሻል:: ይህም ዳግማዊ ልደት ይባላል:: “...ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም:” (ዮሐንስ ወ/ 3÷3) ለመሆኑ <u>ዳግመኛ ተወልደሃል?</u> መቼ? ይህን ሳታረጋግጥ አትረፍ!!

ሌላው:- የልባችን ሃሳብ÷ የአፋችን ቃልና ተግባሮቻችን ሁሉ ወደ ፍርድ የሚቀርቡ መሆናቸው ነው:: የስንፍና ቃሎች÷ከንቱ ቀልዶች÷ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ማንሣት÷ስድብ÷ብልግና÷ዝሙት÷ማመንዘር÷ስርቆት÷መግደል÷ጥንቆላ÷ከእግዚአብሔር ሌላ ማምለክና የመሳሰሉት በጌታ ፊት አስጸያፊ ስለሆኑ÷ ለፍርድ ቀን ይመዘገባሉ:: በተጨማሪ: ግብዝነት÷ አስመሳይነት÷ ቁጣ÷ ጥላቻ÷ ስካር÷ርኩሰት÷ቅናት÷ምቀኝነት÷አመጸኝነት÷ራስ ወዳድነት÷ተዕቢት÷ማጉረምረም÷ ከሐዲነትና ማንኛውም ከትዳር ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ተግባር ፍርድ የሚያስከትሉ ናቸው::

“መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ÷እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን ብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና::” (2ቆሮንቶስ 5÷10)

☛ ስለዚህ ወገኔ ሆይ! ሁሉን የሚያውቅ÷ሁሉን የሚችልና በሁሉም ቦታ የሚገኝ እግዚአብሔርን ችላ በማለት በራስህ ላይ አትፍረድ:: በመጀመሪያ ዳግመኛ መወለድህን አረጋግጠህ ተረዳ:: ከዚያም ጌታ እየሱስን አዳኝህ አድርገህ ስትቀበል ወደ ልብህ የሚገባውን መንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ በየዕለቱ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር:: ********************************************

<u>የንስሐ ፀሎት:-</u> እግዚአብሔር ሆይ÷ ልጅህን እየሱስን ለደኅንነቴ አምኜ እቀበላለሁ:: በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ጻፈኝ:: ከዛሬ ጀምሮ አንተን በመፍራት ከኃጢአት ርቄ መኖር እፈልጋለሁና ርዳኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን::

እየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::